የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

# የጓሊት ጉዞ አገራችንን ይበታትናል

ለዴሞክራስያዊ ስርዓት ለአንድነት የሚካሄደው ፖለቲካዊ ትግላችን የጓሊት ለመዘረር በመንገዳገድ ላይ ባለበት ባሁኑ ሁኔታ አንዳንድ ጽንፈኞች በግራም በቀኝም በማዋከብ እየተፈታተኑት ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችም ይህንን ሁኔታ ለመጋፈጥ የጀመሩት ትግል በእጥፍ ድርብ ማጠናከር ሊኖርባቸው ነው። የአገራችን የፖለቲካ መድረክ እነዚህ ጽንፈኞች እንዳይቆጣጠሩትና ከምን ጊዜውም የከፋ የአገር መበታተንና የወገን መተላለቅ አደጋ እንዳይከተል የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች በመተባበር ትግሉን አቅጣጫ ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ትግል ተጠናክሮ መውጣትና አለመውጣት የአገራችንን የወደፊት ዕድል የሚወስን ይሆናል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ እነዚህ አድርባይ ጽንፈኞች የኢትዮጵያ ህዝብን ትግል በያዙት ጠማማ መንገድ ማዋከብ ከቻሉ የአገራችን ፖለቲካ የጓሊት ጉዞ አይቀሬ ከመሆኑም በላይ የሚያስከትለው መዘዝም በቀላሉ የሚፈወስ አይሆንም። ስለሆነም፣ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝን ለማንበርከክ በመደረግ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች የተናጠል ትግል እንዲሰምር ከተፈለገ በቅድሚያ በጋራ በመሰባሰብ ሁሉም ዓይነት ጽንፈኝነትን በመታገል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚበሰርበትን ሁኔታ ማመቻቸት መቻል አለበት። በዚህ መንገድ ህዝብን ከህዝብ ለማባላት የሚፍጨረጨሩትን ጽንፈኞች በቀላሉ ማግለልና እርቃናቸውን ማስቀረት ይቻላል። ይህንን ካልን ዘንዳ ህዝባዊ ትግሉን የጓሊት ለማስኬድ በመጣጣር ላይ ስለሚገኙት አፍራሽ ኃይሎች የምንለውን ቀጥለን እናቀርባለን።

"አህያውን ፈርተው ዳውላውን" እንዲሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሁሉም የተውጣጣ አምባገነን ገዢ መደብ እያለ ህዝብን ከፖለቲካ ድርጅት ሳይለዩ እንደ ህዝብ በጠላትነት ፈርጀው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች እየተበራከቱ መምጣታቸውን ካስተዋልን ቆየት ብለናል። እነዚህ ጽንፈኛ ፖለቲካ አራማጆች እንደ ፀሓይ ያፈጠጠ ተጨባጭ ማታገያ ምክንያት ሞልቶ-ተርፎ እያለ ፈጠራን ስልት በማድረግ፣ ህወሓት/ኢህአዴግ ለሥልጣን ማራዘምያ ብሎ በህዝቦች መካከል የሚፈጥረው ከፋፋይ ጊዜያዊ የጠላትነት ቁርሾ ሲጠቀሙበት ይታያሉ። ይህ ችግር በአንዳንድ አከባቢዎች ቢታይም መሠረታዊ የሆነ ቅራኔ በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል አለ ብለን አናምንም፣ አይኖርምም። ሆኖም ግን ዛሬ ህወሓት/ኢህአዴግና ሌሎች መሰሎቹ በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ቅራኔ ያለ እያስመሰሉ 'የከፋፍለህ ግዛ' ዓላማቸውን ለማሳካት በመሯሯጥ ላይ ናቸው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ያለውን ስር የሰደደ የአንድነትና የመተሳሰብ ትስስር ለመበጠስ ቀላል አይሆንም። ይህንን እውነታ በመሳት በአሁኑ ሰዓት የትግራይ ህዝብን ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ለመነጠል እየተደረገ ስላለው አደገኛ እንቅስቃሴን ኣስመልክቶ አንዳንድ ጭብጦችን እያነሳን ወደ ማሳየት እናዘግማለን።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የትኩረታችን ማእከል የሆነው በሚያዝያ ወር 2001 ዓ.ም የቀረበው የጄኔራል ኃይሌ መለሰ ባለ 28 ገጽ ጽሑፍ ነው። በመሠረቱ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) እያንዳንዱ ጽንፈኛ በግሉ ለሚጽፈው በራሪ ጽሑፍ መልስ መስጠት

ፍላጎትም ሆነ ዓላማ የለውም። ለወደፊትም ከግለሰቦች ጋራ እንካ-ስላንትያ ውስጥ አይገባም። ሆኖም ግን ጄኔራል ኃይሌ መለሰ ላቀረቡት ጽሑፍ መልስ መስጠት ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል። ምክንያቱም፣ ጄኔራሉ በደርግ ጊዜ በአገራችን የሥልጣን እርከን ውስጥ ከነበራቸው ቦታ አንፃር ፅሁፉ ሲመዘን በርካታ ወገኖቻችንን በጥላቻ መንፈስ ሊበክል የሚችል ሆኖ ስላገኘነው ነው።

ወደ ዋና ዋና ጭብጦች ከማምራታችን በፊት ግን ት.ዴ.ት. በህወሓት/ኢ.ህአዴግ ላይ ያለውን አቋም ባጭሩ ማስጨበጥ ተገቢ ይሆናል።

ት.ዴ.ት የህወሓት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ፀረ-ህዝብና ከፋፋይ አገር አፍራሽ ነው ብሎ ያምናል። ይህ አገዛዝ በምንም መልኩ ኢ.ትዮጵያና የኢ.ትዮጵያ ህዝቦችን ሊያስቀድም እንደማይችል፣ ሀገራዊና ህዝባዊ ጥቅሞችን በተደጋጋሚ አሳልፎ የሰጠ፣ የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች በጠራራ ፀሃይ የገፈፈና ያስገፈፈ፣ የደፈረና ያስደፈረ ኃይል ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ይህ ኃይል በህዝባዊ ትግል እንጂ በምርጫ ካርድ ሥልጣን ያስረክባል ብሎ ፈጽሞ አያምንም። ባገር ላይ ክህደት ከመፈጸሙም በላይ በህዝቦች መካከል ቅራኔ በማስፋፋት የሥልጣን ዕድሜውን ማራዘም እንደ ዓቢይ ዓላማ ይዞ የሚንቀሳቀስ ኃይል መሆኑንም ያውቃል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አንዳንድ ሓላፊነት የማይሰማቸው ጭፍን አክራሪዎች እንደሚያራግቡት የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንድ ናቸው ብሎ አያምንም ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን አመለካከት ይቃወማል፤ ይታገለዋልም።

በማነኛውም መልኩ ህዝብና የፖለቲካ ፕሮግራም ነድፎ ለራሱ ዓላማ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ አንድ ሊሆኑ አይችሉም፣ ሆነውም አያውቁም። በመሆኑም የትግራይ ህዝብ ከተቀረው የኢ.ትዮጵያ ህዝብ የተለየ መንፈስ ያደረበትና ከህወሓት/ኢ.ህአዴግ ጋር በፕሮግራምና በዓላማ ተሳስሮ የሚጓዝ እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ጭብጥ አልባ ጭፍን እምነት ከመሆን ያለፈ ሊሆን አይችልም። የትግራይ ህዝብና ህወሓት/ኢ.ህአዴግ በእምነትም በዓላማም አንድ ሊሆኑ አይችሉም፣ ሆኖውም አያውቁም። ስለሆነም፣ የእያንዳንዱ አምባገነን ባህሪ እንደሚመሰክረው የህወሓት አምባገነኖችም “ህዝብ የሰጠን አደራ” የሚሉትን ነገር አምነን ካልተቀበልን በስተቀር የትግራይ ህዝብ ከህወሓት ጋር አንድ አመለካከት ሊኖረው አይችልም። ህወሓት ከትግራይ ተመርጫለሁ ብለዋልና የጋራ አመለካከት አላቸው የሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርስ ወገን ካለ ደግሞ፣ ህወሓት/ኢ.ህአዴግ መላው የኢ.ትዮጵያ ህዝብ መርጦኝ ነው ሥልጣን የተረከብኩት እያለ ስለሆነ፣ ይህንን ፕሮፓጋንዳም አብሮ መቀበል የግድ ሊሆን ነው። በምርጫ 1997 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ህወሓት/ኢ.ህአዴግ ከ138 ወንበር ውስጥ ቅንጅት ዘንግቶ ተወዳዳሪ ባላቀረበበት ቦታ ላይ የተገኘ አንድ ወንበር ብቻ ነበር ያሸነፈው። ጄኔራሉና መሰሎቻቸው እንደሚሉን የትግራይ ህዝብና ህወሓት አንድ ቢሆኑ አዲስ አበባ ነዋሪ የሆነው የትግራይ ተወላጅ ቅንጅትን ለምን መረጠ? የሚለው ጥያቄ ተገቢ መልስ ማግኘት አለበት።

ት.ዴ.ት ይሁን ፖለቲካውን በቅጡ የሚከታተሉ ወገኖች ህወሓት/ኢ.ህአዴግ በትግራይም ሆነ በሌሎች ክልሎች በህዝብ ይሁንታ ተመረጠ ብለው አያምኑም። የ1997 የግንቦት 7 ምርጫ ውጤትንም አይቀበሉም። ስለሆነም፣ ህወሓት/ኢ.ህአዴግ የማንም ህዝብ ውክልና የለውም ብለው ያምናሉ። ይህ ኃይል ከጅምሩ የህዝብን ሥልጣን ለመንጠቅ ራሱን አዘጋጅቶ የተቀመጠ እንጂ በምርጫ ሳጥን የህዝብን የሥልጣን ባለቤትነት አላረጋገጠም ለወደፊትም አያረጋግጥም። ይህ ዓይነት አምባገነን ባህሪ የተላበሰ በመሆኑም ለትግራይ ህዝብ የተለየ ርህሩህ ልቦና ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ጅልነት ነው።

ይህንን ካልን ዘንዳ፣ የትግራይን ህዝብ ሞራል ለመንካትና በሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ እንዲጠላ ለማድረግ ሲካሄድ የቆየና አሁንም ፍጥነት፣ ጥልቀትና ስፋት ተሰጥቶት በመሰራጨት ላይ ያለው መርዘኛ የጽንፈኞች ፕሮፓጋንዳ ላይ ያለንን ትችት ቀጥለን እናቀርባለን።

ከዚህ በፊት ህወሓት/ኢህአዴግ ግፈኛውን የደርግ አገዛዝን ገርስሶ በራሱ ግፈኛ አገዛዝ በተካ ጥቂት ዓመታት የትግራይን ህዝብ እንደህዝብ የሚዘልፍ ከግል ጋዜጦች በተሰበሰበ መረጃን ዋቢ በማድረግ የማጥላላቱን ቀለም በማጉላት አሰፋ ነጋሽ አንድ ጥራዝ ነገር አሰራጭቶ እንደነበረ የሚታወስ ነው። ከዛ ቀጥሎ ፕ/ር ጥላሁን ይልማ "የትግራይ ህዝብ ካንሰር ስለሆነ ተቆርጦ መጣል አለበት" በማለት ሰፊ ሐተታን ያካተቱ መጣጥፎች በትኖ ነበር። ብዙም ሳይቆይ የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር (ኢአግ) ብሎ ራሱን የጠራ በኦክላንድ የተቋቋመው የፖለቲካ ድርጅት በመተዳደርያ ደንቡ ውስጥ እንኳን ትግሬ ከትግሬ ጋር የተጋባ የፓርቲው አባል እንደማይሆን በይፋ ያወጀበት ሁኔታም ታዝበናል። በ1995 እ.ኤ.አ በዋሽንግቶን ዲሲ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፀረ-ኢህአዴግ ሰላማዊ ሰልፍ በጠሩበት ጊዜ "ሊቀ መምህሩ" ዶ/ር አክሊሉ ትግሬዎች የሚሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ አልገኝም በማለት ተሳትፎውን አሻፈረኝ ያሉበት ሁኔታ እንደነበረም የምናስታውሰው ሃቅ ነው። በጥላቻ ፖለቲካ ስለደነዘዙ አይገባቸውም እንጂ ከፋፋይ ስልት በማራመዳቸው ለኢህአዴግ ባለውለታዎች ናቸው።

ደግነቱ ከዚነህ ጽንፈኛ ፖለቲካ አራማጅ ኃይሎች ውስጥ አንዳንዶቹ በኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ያላሰለሰ ትግል የፖለቲካ አቋማቸው በመሽመድመዱ መክሰማቸው ነው። ቢሆንም፣ እንደ አሰፋ ነጋሽ ዓይነቶቹ በጥላቻ ፖለቲካ የታወሩ ደካማ ግለሰቦች በትግራይ ህዝብ ላይ ያላቸውን የመረረ ጥላቻ እያራገቡ ይኸው እስከዛሬ ዘልቋል። እጅጉን የሚያሳዝነው ግን የነአሰፋ ነጋሽ ቀረርቶ ሳይሆን የቀድሞ የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል አባል የነበሩ ብ/ጄኔራል ኃይሌ መለሰ በፈቃዳቸው የዚህ የከረፋና አገር አፍራሽ የጥላቻ አራማጆች ካምፕን መቀላቀላቸው ነው።

በመሠረቱ አንድ የኢትዮጵያ ጄኔራል፣ ህዝብና የፖለቲካ ፓርቲን ለይቶ የማየት ዓቅም ያንሰዋል የሚል ግምት አድሮብን አያውቅም ነበር። ሆኖም ከደርግ ውድቀት ወዲህ ሁሉም ነገር ግልብጥብጡ እየወጣ የተገነዘብንበት ብዙ አጋጣሚዎችን ስላየን የጄኔራሉ የዘር ጥላቻ አራጋቢ ሆኖ መገኘት ቢያሳዝንንም አላስገረመንም። ምክንያቱም በኢሠፓ ዘመን ፓርቲም፣ መንግሥትም፣ ህዝብም እንደ አንድ አካል ይቆጠር ስለነበረ ትምህርቱን ከዛ መቅሰማቸው ከፅሑፋቸው የተገነዘብነው ሃቅ ነውና። ባይሆን ኖሮ ጄኔራሉ ህወሓትንና የትግራይን ህዝብ በጅምላ በዘር ጥላቻ ለመወንጀል አይነሳሱም ነበር። የዘር ጥላቻ አራማጆችን ሲጠሉ መጥላት ያለባቸው የዘር ጥላቻ አራማጆችን ብቻ ሳይሆን የሚያራምዱትን የዘር ጥላቻ ፖለቲካንም ጭምር መሆን ነበረበት። ጄኔራል ኃይሌና የአመለካከት ተጋሮዎቻቸው ግን የጠሉት የዘር ጥላቻን ሳይሆን የዘር ጥላቻ አራማጆችን ነው። ባይሆን ኖሮ እነሱ ራሳቸውን ከዘር ጥላቻ አባዜ ይላቀቁ ነበር። ከዘር ጥላቻው አዘቅት ራሳቸውን ለማውጣት ባለመቻላቸው ግን በአቋም ደረጃ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋር የሚለዩበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። በዚህም የህወሓት/ኢህአዴግ ዱላ አቀባዮች በመሆን ያገለግላሉ።

ሃቁ ግን እንዲህ ነው። አንድ የፖለቲካ ድርጅት መጥፎም ይሁን በጎ የሚያምንበት የፖለቲካ ፕሮግራም ነድፎ ያንን ለማተግበር በነደፈው ፕሮግራም ዙርያ ሊሰባሰቡ የምችሉ ሰዎችን እየመለመለ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚታገል በመሆኑ፣ አንድ ህዝብ እንደ ህዝብ በሙሉ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አባል ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር አይችልም። የትግራይ ህዝብ ከዚህ የተለየ አይደለም። ስላልሆነም፣ የትግራይ

ተወላጆች በሁሉም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እንደየእምነታቸው ተሰልፈዋል፣ እኩል ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ጋርም መስዋእትነት ከፍሏል፣ እየከፈሉም ናቸው። ይህም የሚያሳየው ትግራይ ህዝብ እንዳለ የህወሓት አባል አለመሆኑና ሊሆንም እንደማይችል ነው። ይህንን ሓቅ ብ/ጄኔራል ኃይሌ መለሰ ከማንም በላይ ሊረዱት የሚገባ እውነት ነበር። በደርግ አገዛዝ ዘመን ህወሓትን በመፋለም ከጄኔራሉ ጋር በየግንባሩ የተሰለፉና ውድ ህይወታቸውን የሰጡ የትግራይ ተወላጅ እንደ ነበሩ (እነሱም በሙሉ ሰረጎ ገቦች ነበሩ ካላሉን በስተቀር) ለጄነራሉ እኛ መንገር ያለብን ምስጢር አይደለም።

ከዚህም አልፎ ከአንድ ጄኔራል ይጠበቃል ብለን የምናምነው ህዝብን እንደ ህዝብ በዘረኝነት መፈረጅ ሳይሆን፣ የተካነውን ሙያ ትጥቅ በማድረግ ህዝብን ባንድነት አስተባብሮ ከፋፋዩን ኃይል በግንባር ገጥሞ መፋለምን ነበር። አለመታደል ሆነና ግን ጄኔራሉ የትናንሾቹ ጎራ ውስጥ ራሳቸውን ለማስቀመጥ መርጧል።

ይህንንም ከላይ እንደገለጽነው ጄኔራሉ **“የትግራይ ህዝብ የሚያሳየው ሁኔታ፣ ይሁንታ? ወይስ መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ?** በሚል ርእስ ሚያዝያ 2001 ዓ.ም ያሰራጩት ፅሑፍን በማመሳከር ለማሳየት እንሞክራለን።

በዚህ ፅሑፋቸው ውስጥ ጄኔራል ኃይሌ የትግራይ ህዝብና ህወሓት በአንድ ሙቀጫ ውስጥ ከተው ፈጭቷል። በመሆኑም በፅሑፉ ላይ ያለንን ትችት አጠር አርገን እናቀርባለን።

በመሠረቱ አንድ ሰው ህዝብን እንደ ህዝብ ለመተቸት ከመነሳሳቱ በፊት፣ አስቀድሞ ራሱን መመርመር ይኖርበታል የሚል እምነት አለን። ጄኔራል ኃይሌም የትግራይን ህዝብ በተጠቃሚነትና በህወሓት/ኢህአዴግ ዓላማዎች አራማጅነት ለመወንጀል ከመሽቀዳደማቸው በፊት ያንን ህዝብ እንደ ህዝብ ለመወንጀል የሚያስችል የሞራል ብቃት ይኖራቸው እንደሆን ራሳቸውን መመርመር ይገባቸው ነበር። ጄኔራሉ በደርግ አገዛዝ ጊዜ ለከፍተኛ መዓርግ የደረሱ ናቸው። ሙያውም፣ ትጥቁም፣ ሠራዊቱም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በእዛቸው ሥር ነበር። ሆኖም ግን እስከ ዕለተ-ሞቱ ሲገለገሉበት የነበረ ሥርዓት ፈራርሶ በህይወት እስኪያመልጡ ድረስ አንድ ኢትዮጵያዊ ትውልድ እሳቸው በጄኔራልነት ባገለገሉት አገዛዝ ሲመተር የሞራል ግዴታቸውም ሆነ ህዝብ የጣለባቸውን አደራ መወጣታቸውን የሚያሳይ የቀረበ መረጃ የለም። ቢሆንም ግን ዛሬ በህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ሥር የሚማቅቀውን የትግራይን ህዝብ ከአምባገነኑ የህወሓት አመራር ጋር አዳብለው ለመጨፍጨፍ ከመሞከር አልታቀቡም።

“ከበሮ በሰው ሲያዩት ሲያምር፣ ሲይዙት ያደናግር” ይባል የለ! ጄኔራል፣ ምን ነው እርሶዎ ሙያውም፣ ሓላፊነቱም፣ ትጥቁም፣ ሠራዊቱም በእዝዎ ሥር እያለ ትውልድና አገር እየጠፋ ነው ለማለት ሞራል አጥሮዎት እንደነበረ እያወቁት ዛሬ ትጥቅ አልባ፣ ሥልጣን አልባ፣ ሆኖ በአምባገነኖቹ የህወሓት መሪዎች የጭካኔ አለንጋ እየተገረፈ፣ አፉ እንዳይናገር፣ ጆሮው እንዳያዳምጥ፣ ጋዜጣ እንኳን እናዳያይ የተደረገውን የትግራይን ህዝብ እንዲህ ለማብጠልጠል ቃጡ? ሞራልዎስ እንዴት ተቀበለው? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን።

ይህንን ብለን ወደ ፅሑ ይዘት ስንገባ የጄኔራሉን ፅሑፍ መስመር በመስመር እየተከታተልን ግድፈቱን ለመተቸት ብንሞክር የሚወስድብን ጊዜና ቦታ ከፍተኛ ስለሚሆን አንሞክረውም። ስለሆነም ለናሙና ያክል ብቻ የተወሰኑ ጭብጦችን በማንሳት አንባቢ አጠቃላዩን ትርጉም እንዲጨብጥ በማረግ ለመወሰን እንገደዳለን።

ጄኔራል ኃይሌ መለሰ፣ በመጣጥፋቸው ውስጥ ገጽ-1 ላይ እንደሚከተለው አስፍረዋል።

> "መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ ስል ደግሞ ከላይ በአጭሩ የተመለከቱትን በታሪክ ሲያፋራርዱና በትውልድ ሲያጠያይቁ የሚኖሩ <u>ግፍና በደሎች መፈጸማቸውን እያወቀ</u> በይፋ ቀጥሉበት ለማለትም ይሁን የእስካሁን በቃችሁ ብሎ ለማስቆም እንዳይችል መንገዱ ላይ ያቆሙበት ምልክት የነሱ ብቻ አረንጓዴ የሌሎቹ ግን አደጋ ያለበት ቀይ ሆኖ እንዲታየውና ትክክለኛ አቅጣጫውን እንዳይለይ ህልናውን የጋረደው አንድ የተቋጠረ ነገር መኖሩን ለማመልከት ስል የተጠቀምኩበት ቃል ነው። ……………………ከዚህ አንፃር ከተገናዘበ የትግራይ ህዝብ ዝምታ (አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አቤት አይልም እንደሚባለው) ከይሁንታ ጋር የሚያገናኘው የሚስጢር በር፣የሚግባባበት ቋንቋና የሚደጋገፍበት ጎን አለው የሚያሰኝ ትርጓሜ ብሰጥ የተሳሳትኩ አይመስለኝም።" (መስመር የኛ)

እዚህ ላይ ….ግፍና በደሎች መፈጸማቸውን እያወቀ…. የሚለውን አንባቢ ልብ እንዲለው እንፈልጋለን።

ቀጠለው በገጽ-7 ደግሞ እውነቱ ሾልኮ ሲወጣ፣

> "…የትግራይን ህዝብ መደበቅያ ምሽግና መግደያ መሳሪያ አድርገው በመገልገል ላይ ያሉት ወያኔዎችም…።….እንዲህ ያለውን ከባድ ጭንቀት እየተከላከሉ የሚኖሩት ለእነሱ ጊዜያዊ እፎይታ የሚሰጥ ጭንቀት እየፈጠሩ የትግራይ ህዝብ እንዲጨነቅ በማድረግ ነው።" ይላሉ። "1. የትግራይ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር በመድረክ ተገናኝቶ በጋራ ጉዳዮች ላይ እንዳይወያይ፣ በማህል አገር ስለሚደረግ ማናቸውም መረጃወች እንዳይደርሱት፣ ለዘመናት አብሮት የኖረውንና ያኗኗሪውን አብሮነቱን ግምት እንዲያሳጣው፣ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ሲገነባ የኖረውን የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ፍቅር ከጥላቻም አልፎ በጠላትነት እንዲፈርጀው፣ በአጠቃላይም ኢትዮጵያዊነቱን እንደውርደት ትግራይነቱን ደግሞ እንደ ልዩ ፍጡርነትና ወርቅ ሕዝብነት አድርጎ እንዲያየው የሚያደርግ ርብርቦሽ ያለማቋረጥ በቀጣይነት እየተካሄደ ነው።" በማለትም ያክሉበታል።

እነዚህ ሁለት ጥቅሶችን ስንመለከት ጄኔራሉ የትግራይ ህዝብ ተሸክሞት ያለ ፍዳ ምን እንደሆነ እንደሚያውቁ፣ ግን በምን ቸገረኝነት የትግራይን ህዝብ ለማንኳሰስ እንደተነሳሱ ግንዛቤ እናገኛለን። ለመሆኑ ጄኔራሉ በትክክል እንዳስቀመጡት "በማህል አገር ስለሚደረግ ማናቸውም መረጃ እንዳይደርሱት" የተደረገ ህዝብ "ግፍና በደሎች መፈጸማቸውን እያወቀ" የሚባለው ውንጀላ እንዴት ተደርጎ ይሆን?

እውነት ነው፣ ለትግራይ ህዝብ ነፃ ጋዜጦች አያስፈልጉትም ተብሎ በህወሓት መሪዎች በይፋ የተፈረደበት በመሆኑ ሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ የሚያገኘው ዓይነት መረጃ አያገኝም። አያገኝም ብቻ ሳይሆን አግኝቶ፣ ባገኘው መረጃ ላይ በሽኩሽክታ እንኳ ሲወያይ ቢደረስበት ከየት አገኘኸው? ተብሎ ምንጩን እንዲያወጣ ቁም ስቅሉን እንደሚያሳዩት የታወቀ ነው። የሩቁን እንተወውና በራሱ በቀበሌው ውስጥ ዓይኑ እያየ ስለደረሰው ግፍ ቢመሰክር ወይም ከጎረቤቱ ጋር አንስቶ ቢወያይ የህወሓት ደህንነት ቢሮ እየተጠራ ደርግ፣ ኢዲዩ፣ ቅንጅት፣ ትምክህተኛ፣ ዛሬ ደግሞ ግንቦት ሰባት፣ …..ወዘተ እየተባለ ቁም ስቅሉን ከማየት አልፎ መሬቱን እስከመነጠቅ በሚደርስ አይቀጡ ቅጣት እየተቀጣ ያለ ህዝብ ነው። ጄኔራሉ በፅሑፋቸው በገጽ-8 ቁጥር 4 ላይ "የትግራይን ሕዝብ በከፍተኛ ስጋት አስጨንቆ በመያዝ ሌሎች ጠቃሚ አማራጮችን በትክክል እንዳያይ እያደረጉት ናቸው።" በማለት በትክክል ያስቀመጡት እውነት የሚመሰክረውም ይህንን ሐቅ ነው። ሆኖም ግን ይህንን እውነታ ጠንቅቀው እያወቁ ጄኔራሉ

በፅሑፋቸው ገጽ-3 ላይ "…..አጠያያቂ የሆነው ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን በቁርጠኝነት ከሚዋደቁት ይልቅ ሊያጠፏቸው አቅደው የተነሱትና ተደራጅተው የዘመቱት በእጥፍ ድርብ ከመሆናቸው በተጨማሪ የትግራይን ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ አግኝተው ያን ሁሉ ውድመትና እልቂት ማድረሳቸው ነው።" የሚል አስፍሯል።

ጄኔራሉ አንዱን ይዘው ቢከራከሩ መልካም ነበር። ባንዱ ገጽ ያስቀመጡትን በሌላ ገጽ እያፈረሱ መሄዳቸው ግን ግራ ያጋባል። የትግራይ ህዝብ መረጃ እንዳያገኝ መከልከሉን ካመኑ፣ ሙሉ ድጋፍ ሊሰጥ የቻለው በምን ላይ ተመርኩዞ ነው? የሚለውን ጥያቄ ሊመልሱት ይገባል። የትግራይ ህዝብም ሆነ ማንኛውም ሌላ ህዝብ ሙሉ ድጋፉን ለመስጠትም ሆነ ለመንሳት ብቁ መረጃ ማግኘት ይኖርበታል። ፍርድ መስጠት የሚቻለውም ባገኘው መረጃ ላይ ተመርኩዞ በሚወስደው አቋም ነው። ስለሆነም የጄኔራሉ ውንጀላ ቦታ የሚሰጠው አይሆንም።

ለመሆኑ በአንድ የወጣለት አምባገነን አገዛዝ ሥር የሚኖር ህዝብ ትክክለኛ መረጃ ቢኖረው በፈለገው ሰዓት የፈለገውን አቋም ለመውሰድ ይችላልን? የሚችል ቢሆን ጄኔራል ኃይሌ መለሰ ሲያገለግሉት የነበረው የደርግ ሥርዓትን ተፈጥሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያውቀው ስለቀረ ነበር በአደባባይ ወጥቶ ለልጆቼ ሬሳ የጥይት ዋጋ አልከፍል ለማለት ያልቻለው? ወይስ ጄኔራሉ እሱንማ እኔ ራሴ የተገለገልኩበት አገዛዝ ስለሆነ አታንሱብኝ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ተቀብሎት ስለነበረ ነው በማለት ሊደልሉን እየቃጣቸው ነው?

ጄኔራል፣ በአምባገነኖች አገዛዝ ሥር ወድቆ የመደራጀት መብት የተነፈገ ህዝብ በአንድ ጀንበር ተነስቶ ተቃውሞ ለማሰማት አይችልም፣ ቢያሰማም ይመታል እንጂ የሚያመጣው ፋይዳ አይኖርም። የግንቦት 1997 ዓ.ም የምርጫ ውጤት በተጭበረበረ ማግስት ብቁ ድርጅታዊ አመራር ባለማግኘቱ ከተመታው ህዝባዊ ንቅናቄ የምንማረውም ይህንን ሃቅ ነው። የሌሎችን ትተን የደርግና የህወሓት አምባገነን መሪዎችን ግፍ ብንወስድ፣ በሁለቱም እየተመታ ቁምስቅሉን አይቶ አሌ የማይባል የህይወትና የንብረት ስብራት የደረሰበትና ገና ከደረሰበት የጎልናና የመንፈስ ስብራት (ትራውማ ) ያላገገመ የትግራይ ህዝብን የህወሓት መሪዎች መስሪ ዓላማ ደጋፊና አራማጅ ነው ብሎ መክሰስ ከሞራል ዝቅጠት ውጭ ሌላ የሚያመላክተው ነገር አይኖረውም። ለነገሩማ "በሰው ቁስል እንጨት ክትትበት" ይባል የለ ጄኔራል! እርሰዎ እያደረጉት ያለም ያ ነው። ባይሆንማ ያ ህዝብ ያለፈበትና እያለፈበት ያለውን ሰቆቃ ከርስዎ በላይ ሊገነዘበው የሚችል ባልኖረ ነበር። ምን ይደረግ ቢያሳዝንም እርስዎም የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነን መሪዎች በቀደዱትና በሚያራምዱት የዘር ፖለቲካ ዘለው ስለገቡበት ምንም ሊያደርጉት ያልቻሉት ችግር እንዳለብዎት በሚገባ እንረዳለን። ጄኔራል! እርሶና መሰሎችዎ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋራ የይዘትም ሆነ የዓይነት ልዩነት የላቹህም። ልዩነታቹህ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋራ በጋራ ሊያሰራቹህ የሚችል የዓላማ ወይም የአቋም ሳይሆን የሥልጣን ሽኩቻ ነው። እርስዎ በአቋም ደረጃ የሚያራምዱት የህወሓት/ኢህአዴግን አቋም በመሆኑ የሚያጣላቹህ ሥልጣን ብቻ እንደሆነ ጽሑፍዎ ፍንትው አርጎ ያሳያል።

የጄኔራል ኃይሌ ክስ በዚህ አያበቃም በገጽ-6 "…….የትግራይ ህዝብ ግን ባድሜን ብቻም ሳይሆን እነዚህ ሁሉ የእኔም ናቸው ብሎ ካልተከላከለላቸውና አሳልፈው ከመስጠትና እየቆረሱ ከመሸጥ የማይመለሱትን ልጅ መሰል ጠላቶች ካልተጋፈጣቸው ዘብ ቁሞ የሚጠብቃቸው የትኛዎቹንና መቼ ሊሆን ነው?"

በማለት ጥያቄ አቅርቧል። በመሠረቱ የትግራይ ህዝብ ሻዓቢያ ኢትዮጵያን ለመውረር በዝግጅት ላይ ነው ብሎ ለህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ጦርነቱ ከመጀመሩ ዓመት አስቀድሞ ቢያስጠነቅቅም ጦርነቱ እስኪጀመርና ዳር ድንበራችን እስኪደፈር ድረስ ሰሚ ጆሮ ተነስቶት እንደነበረ ሁላችን የምናውቀው ሃቅ ነው። በመሆኑም መጨረሻ ሻዓቢያ ወረራውን እንደፈጸመ ያለውን ይዞ ተጋፍጦ ያስቆመው የትግራይ ህዝብና ምልሻው ብቻውን እንደነበረም የሚታወቅ ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ መደበኛ ሠራዊትን ያመጣው ህዝቡ መስዋእትነት በመክፈል እምቢተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ነበር። መጨረሻ ላይ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ በወገን ደም የተገኘውን ድል እንዴት ለተሸናፊ ጠላት እንደተሰጠም የምናውቀው ነው። ሆኖም ግን የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያዊ ደም የተከፈለበትን የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬቶች በህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ለሻዓቢ ሊቸሩ ሲውጠነጥን በዓይኑ ሥር እየተፈጸመ ያለ ጉድ በመሆኑ እምቢኝ አልሰጥም ብሎ ግብግብ ፈጥሮ እንደነበረ የሚታወስ ነው።

ለሱዳን ተሰጠ የሚባለው መሬትም ቢሆን የትግራይ ህዝብ እንደማንም ኢትዮጵያዊ ለዳር ድንበሩ ቀናኢ በመሆኑ መስዋእትነት እንደሚከፍል መጠራጠርዎ ያሳዝናል። የትግራይ ህዝብ ላገሩ ዳር ድንበር መከበር መስዋእትነት ሲከፍል የኖረና በተግባር ያስመሰከረ በመሆኑ የጀነራል ኃይሌ መለሰን ሰርቲፊኬት አያስፈልገውም። የሆነ ሆኖ ግን እስቲ ጀኔራሉ ሱዳን ሉዓላዊ መሬታችንን ወሮ በመከላከል ላይ ነኝ ብለው ለትግራይ ህዝብ መልእክቱን ያስተላልፉና መልሱን ያኔ እንየው። ለመሆኑ ሌላው ኢትዮጵያዊ ወደ ግንባር ከቶ የትግራይ ህዝብ ባለመሳተፉ ነው ሱዳን መሬታችንን የሚወስደው ወይስ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን በመጨበጡ የትግራይ ህዝብ ሥልጣን ጨብጧልና ከሌላው የበለጠ ሓላፊነት አለበት ነው የሚሉን ያለው? ጀኔራል ሙያው የርሶ ነውና እኛ ይህንን ለርስዎ የምንመክረው ጉዳይ አይሆንም። ለመሆኑ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህሉ ነው በፍልሚያ ላይ ያለው? ጀኔራል! አንድ ህዝብ በሉዓላዊነቱ ላይ የሚሰነዘረውን ማነኛውንም ዓይነት ጥቃት ለመከላከል ዝግጁ ቢሆንም፣ ባለንበት ዘመን አገርን የመከላከል ጦርነት የሚያስተባብር መሪ ኃይል ከሌለ ብድግ ብሎ በየግሉ ወደ ጦር ግንባር መዝመት የተለመደ አይደለም። የዛሬ አያርገውና በድሮ ጊዜ ይህንን ዓይነት ግዳጅ የሚመሩና የሚያስተባብሩት ጀኔራሎች ነበሩ። ይህ ዛሬ የለም። ታዲያ በዚህ ሁኔታ የትግራይ ህዝብ ምን ያድርግ ነው የሚሉት? ከዚህም ውጭ የትግራይ ህዝብ እንደሚያውቁት ምንም መረጃ ላይደርሰው ስለሚችል ለውንጀላ ከመሽቀዳደም ረጋ ብሎ ጊዜ ወስዶ፣ አጥንቶና አስተውሎ ፍርድ መስጠት ከመሳሳት ያድናልና ረጋ ብለው ቢያመዛዝኑ መልካም ነው። በጽሑፍዎ ገጽ-16 ላይ "ወያኔዎችማ በባዳነት የሚያዩትን ቀርቶ የዘመዶቻቸውን እንኳ የሚያዳምጥ ጆሮ ያላቸው አይመስለንም።" ያሉትን እነመለስን ማለትዎ ከሆነ ሙሉ በሙሉ እንጋራዎታለን።

ሌላ ጀኔራሉ በገጽ-18 ላይ "…….ነገር ግን በትግራዊነታቸው የተገደሉ ቀርቶ ታሥረው የተንገላቱ አንድም እንኳ ለማስረጃ ያህል አይገኝም።" የሚሉትን ቀለል አርገን እንየውና መረጃ ለማግኘት ጥረት ካለማረግ የሚከሰት ድክመት ብለን እናስቀምጠው። በመሠረቱ የጀኔራሉ ሓሳብ የተዛባ ቲዎር አለበት። የተገደሉም የታሰሩም የትግራይ ተወላጆች አሉ። አብነት እንጥራ ከተባለ፣ እሳቸው ባገለገሉት አገዛዝ ውስጥ አብረዋቸው በምልሻነትና በወታደርነት ሲያገለግሉ የነበሩ ብዙ የትግራይ ተወላጆች (እነሱ አይቆጠሩም ካላሉን በስተቀር) ተገለዋል፣ ታሥሯል። ከሚያውቋቸውና ከታሰሩት ውስጥ አንዱ ኮሌኔል ፍስሐ ደስታ ናቸው።

የኢህአፓው ኃይም ኃይለሚካኤል የተገደለው በነሱ ታጣቂዎች ነው። በህወሓት/ኢህአዴግ እጅ ወድቀው እስከዛሬ የደረሱበት የማይታወቁት የኢህአፓ አባላት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች አሉባቸው። ህወሓት ከሜዳ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የራሱ ታጋዮች የነበሩትንም ጭምር ገሏል፣ አስረዋልም። ከሁሉም በላይ ደግሞ የትግራይን ህዝብ እንደ ህዝብ የራሱ ጭሰኛና ቁም እስረኛ አድርጎት ይገኛል። ባይከታተሉት ነው እንጂ ቤተ-ሰብ እንዳለ ድራሹን የጠፋበት ሁኔታ ጊዜና ወቅት ጠብቆ የሚዘገቡ አሰቃቂ ታሪኮችም አሉ። በዚህ ነጥብ ዙርያ ከጄኔራሉ ጋር የማያሰማሙን በጣም ብዙ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌም፣ “በትግራዊነታቸው የተገደሉ ቀርቶ ታስረው የተንገላቱ አንድም እንኳ ለማስረጃ ያህል አይገኙም።” ሲሉ፣ በዘሩ የሚገደልና ታስሮ የሚንገላታ ወገን አለ ለማለት የቃጣቸው ይመስላል። እነዚህ ላይ እኛ ከላይ የጠቀስናቸው የታሰሩና የተገደሉ የትግራይ ልጆች ከትግራይ በመሆናቸው ምህረት አልተደረገላቸውም የሚል እምነት አለን። ለአምባገነኖች አገዛዝ የማያመቹ በመሆናቸው ካልሆነ በዘር ማንነታቸው የተገደሉና ታሥረው የተንገላቱ ወገኖች ለመኖራቸውም መረጃ የለንም። ጄኔራሉ የሚያቀርቡልን መረጃ ካለም አብረናቸው ለማውገዝ ዝግጁ ነን። ጠቅለል ባለመልኩ ስናስቀምጠው ህወሓት/ኢህአዴግ ሰውን የሚገድለውና የሚያንገላታው ሥልጣኑ ላይ ሊያደርሰው ከምችለው አደጋ አንጻር እንጂ በዘሩ ነው ብለን አናምን። በዘር ቢሆን ኖሮማ ከላይ የጠቀስናቸውና ያልዘረዘርናቸው የትግራይ ልጆች ባልተገደሉ ነበር።

የተዛባ ቲዎሪ ያልንበት ምክንያትም ያ ነው። እኛ የምናምነው ማነኛውም የዘመናችን አምባገነን ሰውን የሚያስረውና የሚገለው የዛ ወይም የዚህ ዘር አባል በመሆኑ አይደለም። ህወሓት/ኢህአዴግ የሚገድለው ከማንም ይምጣ ከየት ለሥልጣኑ ጠንቅ ነው ብሎ የሚገምተውን ነው። ባይሆን ኖሮ በሥልጣን ቆርሾ ውስጥ ያሳተፋቸውና የሾማቸው የሌላ ብሔር ተወላጆችን በሙሉ በገደለ ነበር። ይህም የሚያሳየው፣ ሰውን የሚገለው ወይም የሚያስረው ከተወሰነ ብሔር በመወለዱ ሳይሆን በሥልጣኑ ላይ ተደላድሎ እንዳይቆይ አደጋ ሊሆንብኝ ይችላል ብሎ ሲገምት ነው። በሥልጣን ከመጣ ደግሞ ከትግራይ በመሆኑ የሚተርፍ ቢሆን ኖሮ አብሮአቸው ታግሎ የአስፈጻሚው አባል የነበረው ስዬ አብርሃ ለእስር አይዳረግም ነበር። በመሆኑም አመለካከትዎ እጅጉን የተዛባ ነው እንላለን።

ሌላው እዚህ ሳንጠቅሰው የማናልፈው ጉዳይ ቢኖር “የትግራይ ህዝብ አይታገልም ያለው” የሚለውን ክስና ውንጀላን ነው። በዚህ ነጥብ ዙርያም የጄኔራሉ ፅሑፍ ውስጥ ከተወሰኑ ግለሰቦች ውጭ ብዙሃኑ የትግራይ ህዝብ “ከወያኔ” እንደወገነ አድርገው ፈርጀውታል። ይህ አመለካከት ግን የጄኔራሉ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማኅበራትም የሚጋሩት ስለሆነ፣ ባጠቃላይ መልኩ ቢታይ የተሻ ግንዛቤ ስለሚያስጨብጥ ጠቅለል አርገን ለማየት እንሞክራለን።

ይህንን ነጥብ ስናነሳ “የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል” የሚለውን የአበው ምሳሌ እንድናስታውስ ያደርገናል። ለጊዜው የትግራይ ህዝብ እየታገለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ወደ ጎን እንተወውና፣ የትግራይ ተወላጆች የትግል አስተዋፅዖን ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚያስገቡት ወገኖች ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህሉን ከጎናቸው ስላሰለፉ ነው? የሚለው ጥያቄን ቢመልሱ የችግሩን ዋና ምንጭ ለማግኘት ይረዳን ነበር። እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት የትግራይ ህዝብ በህወሓት ጉያ ገብቷል እንኳ ቢባል፣ የትግራይ ህዝብ መልካም ተግባራችን፣ የማያወላውል በጎ ዓላማቸውንንና የሚጎናጸፉት ድልን አይቶ

እስኪከተል ድረስ የተቀረውን 94/95% የኢትዮጵያን ህዝብ በማንቀሳቀስ አገሪቱን ከጥፋት ማዳን ቀዳሚ ተግባራቸው አድርገው መወሰድ ነበረባቸው፣ አለባቸውም። ይህንን ማድረግ ሲያቅታቸው የትግራይ ተወላጆች ትግሉን አልተቀላቀሉም የሚል ክስ በመደርደር ብቻ ተግባር አልባ ጩኸት በመጮህ አገርን ከጥፋት ማዳን እንደማይቻል ገና አልተረዱትም። የፉክክር ቤት የምንለውም ለዚህ ነው። እነዚህ ግብዝ ወገኖች በተግባር አገርን ለመታደግ በመታገል ላይ ያሉትን የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራቶች መልካም የትግል አርአያን በመመልከት የነሱን ተምሳሌት በመከተል አገር የማዳን ተግባር ላይ ቢሠማሩ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል ቢረዱ መልካም ነበር። ይህንን መረዳት ስለማይችሉ ግን ለትግሉ እንቅፋት በመሆን ላይ ናቸው። ዴሞክራቶቹ እገሌ መጣ እገሌ ቀረ የሚለውን ቅድመ ሁኔታ አያስቀምጡም። የዓላማ ጽናት ያላቸው በመሆኑ ማንተሳተፈ ማን አልተሳተፈም የሚለውን እንደ ትግል መስፈርት አያስቀምጡም። ይልቁንስ በትግል ሁሉንም ለማሳተፍ እንደሚችሉ በመተማመን ርትዓዊ የሆነ ህዝባዊ ትግል ነው የሚያካሂዱት። ይህ አካሄዳቸው ደግሞ ለድል እንደሚያበቃቸው ጥርጥር የለውም። በመሆኑም በዚህ ተግባራቸው ሊመሰገኑና ሊደገፉ ይገባል። እነዚህ ወገኖች የሚታገሉት የኢትዮጵያ ህዝቦች ዓላማን እግብ ለማድረስ እንጂ ለፉክክር አይደለም። ጄኔራል ኃይሌና መሰሎቻቸውም "የትግራይ ካልታገለ" ፉክክራቸውን አቁመው ላገርና ለወገን የሚበጀውን ተግባር ቢያከናውኑ የበለጠ አስተዋጽኦ ሊኖራቸው እንደሚችል አንጠራጠርምና መወንጀልን ትተው የራሳቸውን ግዴታ ቢወጡ መልካም ነው።

የትግራይ ተወላጆች የትግል ተሳትፎን በሚመለከት ከጄኔራል ኃይሌና የአመለካከት ተጋሪዎቻቸው ጋር የማንስማማበት ጉዳይ አለ። በመሠረቱ የትግል ጥሪ ማቅረባቸው ለትግራይ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለማነኛውም ቢሆን እጅግ የሚደገፍ ነው፣ መቀጠልም አለበት። ጠሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት የሚችሉት ግን ራሳቸውን ከዘር ጥላቻ አባዜ ነፃ ሲያወጡ ነው። የዘር ጥላቻ የተጠናወታቸው ወገኖች የትግል ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ አለማግኘቱ ግን አገባብ ነው። ለወደፊቱም ቢሆን ከማንም ህዝብ አዎንታዊ ምላሽ አያገኙም። የዘር ጥላቻን ለማራገብ ከሆነማ እዛው ህወሓት/ኢህአዴግ አለለት አይደለ እንዴ? ሌላ ዘረኛ ለማንገሥ መታገል አለበት ነው እየተባለ ያለው? ዛሬ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን በመጨበጡ የትግራይ ህዝብ ሲዘለፍ የሚያየው ሌላው ወገን ነገ በኔ ማለቱ አይቀሬ ነው። በመሆኑም ትግሉ የዘር ጥላቻን ከነአካቴው አጥፍቶ የኢትዮጵያ ህዝብን ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚያበቃ መሆን አለበት። የትግሉም አልፋ ኦመጋ መሆን ያለበት ይህ ነው። ይህ በዚህ እንዳለ የትግራይ ተወላጆች በትግሉ ውስጥ አይሳተፉም የሚለው አባባል እንዳለ ከተወሰደ መሠረት አልባ ክስ ነው። በበለጠ ቁጥር መሳተፍ አለባቸው ለማለት ከሆነ፣ ሓሳቡን እንጋራዋለን ብቻ ሳይሆን፣ አቅም በፈቀደ ጥረታችን አብዛኛውን ብቻ ሳይሆን መላውን ከጎናችን ለማሰለፍም ነው፣ መሆንም አለበት። ይህ ግን የትግራይን ህዝብ ለይቶ የሚመለከት ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመለከት ስለሆነ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ከባድ ሥራ ይጠብቃቸዋል። ከተቻለ አንድም ኢትዮጵያዊ ሳይቀር በዴሞክራሲያዊ ትግሉ እንዲሳተፍ ማድረግ ተገቢ ነው።

ከዚህ በተቀረ ግን የትግራይ ተወላጆች በት.ዴ.ት፣ በትግራይ ሶሊዳሪቲ፣ በዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማኅበር ሥር ተደራጅተው የነበሩ፣ በጋሻ ለኢትዮጵያ፣ በዓረና ትግራይ፣ በኢዴህ፣ በኢዴኃኅ፣ በቅንጅት……..ወዘተ ሥር ተደራጅተው እየታገሉ ናቸው። ለነዚህ ታጋዮች እውቅና ላለመስጠት የሚደረገው የማጥላላት ዘመቻ ለዴሞክራሲያዊ ትግሉ ጠቃሚ አይደለም።

በትግል አስመስክሮ እንጂ የነሱን ትግል በማንኳሰስ ጌትነት አይገኝም። እነዚህ ወገኖችን የዘር ጥላቻ የተጠናወታቸው ወገኖች በሚያራምዱት አሉባልታ ሳንደናገጥ ከኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ጋር በመወገን ትግሉን የማጠናከር ሓላፊነታችንን በርትተን እንወጣ እንላለን።

ስለ ዘረኝነት አባዜ ስናነሳ የምንቃወመውና የምንታገለው ሁሉንም ዓይነት ዘረኝነትን ነው። በመሆኑም በአንዳንድ የህወሓት ዓላማ አራማጆች ባለቤትነት በሚንቀሳቀሱ ድረገፆችና ብሎጎች ላይ የሚታዩ የዘር ጥላቻን የሚያራግቡ ፅሑፎችና ፀሓፊዎችንም አጥብቀን የምንኮንን መሆናችን ብቻ ሳይሆን አምርረን የምንታገላቸው መሆኑንም እንዲያውቁት እንሻለን። የህወሓት ደጋፊዎች ቢያደናጉት ዓላማቸው ነውና የሚገርመን ባይሆንም፣ አንዳንድ የዋሆች የህወሓት ዘረኛ አመለካከት ሰለባ መሆናቸው ግን እጅጉን ያንገበግበናል። በነዚህ ጋጠወጦች ክፉ ተግባር የትግራይ ህዝብ መልካም ስምና ስነ-ምግባር ጥያቄ ውስጥ እንዲያስገቡም አንፈቅድምና ዴሞክራት የትግራይ ተወላጆች እነዚህን ጋጠወጦች ያለምሕረት እንዲታገሉዋቸው ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ከዚህ ሌላ በቅርቡ ያልጠበቅነው ርዕዮተ-ዓለማዊ አድማሱ ሰፋ ያለ ነው ሲባልለት የነበረው ግንቦት 7 እ.ኤ.አ ሰኔ 4 ቀን 2009 ዓ.ም በእንግሊዝኛ ባወጣው መግለጫው ላይ “ በኢትዮጵያ የሚገኘው 6% የሚሆነውነ ህዝብ ብቻ **የሚወክለው** ሕገ-ወጡ የህወሓት አገዛዝ ለብቻው የተቆጣጠረው ሥልጣን…….” (ትረጉም የኛ) ሲል ባስቀመጠው አባባል እጅጉን የሚያስከፋ ነው። ምክንያቱም፣ ከግንቦት 7 ከፍተኛ አመራሮች ውስጥ የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምርጫ ምን ይመስል እንደነበረና ቅድመ ምርጫ፣ ምርጫና ድኅረ ምርጫ በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ሥር መኖር ምን ዓይነት ኣሰቃቂ እንደሆነ ከማንም በበለጠ እንደሚረዱ ስለሚገባን ነው። ከነዚህ አመራሮች መካከል አንዳንዶቹ በቅድመ ምርጫ ወቅት ትግራይ ሂደው ህዝባዊ ስብሰባዎች በማካሄዳቸው ህዝቡ ምንኛ እንደታፈነ፣ የህዝቡ ስሜትና የህወሓት ካድሬዎች ፀረ-ህዝብ እንቅስዋሴዎች ምን ይመስሉ እንደነበረ በአካል ተገኝተው የተገነዘቡ ናቸው። በመሆኑም፣ በዓይናቸው ያዩትን መመስከር አቅቷቸው የህወሓት አምባገነን ቡድን የትግራይ ህዝብ ወኪል ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው አስተዛዛቢ ይሆናል።

ግንቦት 7 ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚያወጣቸው የቅስቀሳ ጽሑፎች ባጠቃላይ ሲገመገሙ ሃቅነት የጎደላቸው ከመሆን ባሻገር የትግራይ ህዝብና ህወሓትን ለይተው ያላስቀመጡ፣ ግፋ ቢል የትግራይ ህዝብ ከትርፍራፊው ተጠቃሚ ነው የሚል ስሜት የሚቀሰቅስና በጭቁን ህዝቦች መካከል አላስፈላጊ የእርስ በርስ መጠራጠርና የጎሪጥ መተያየት ስሜትን የሚፈጥር መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ የሚፈጠሩ ስሜቶች ደግሞ ህዝባዊ ትስስርና ትግልን ከማኮላሸቱ ኣልፎ በቀላሉ ሊቀረፉ የሚችሉ ባለመሆናቸው ላገራችን ዘለቄታዊ ሰላምና መረጋጋት፣ ብሎም ለህልውናዋና ላንድነቷ ከፍተኛ እንቅፋት ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ከወዲሁ ግልጽ ሆኖ ሊታወቅ የሚገባ ጉዳይ ነው። በቅርበት ደግሞ ኣምባገነኑ ኢህኣዴግን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ጉዳት እንጂ ጥቅም ኣይሰጡም። ባጭር አነጋገር “ህወሓት ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ነው፣ የትግራይ ህዝብ ማለትም ህወሓት ማለት ነው” የሚለው የህወሓት አምባገነን መሪዎች ግብዝ የብልጣብልጥነት አባባል በግንቦት 7 ይሁን በሌሎች ሰዎች ተቀባይነት አግኝቶ ባይስተጋባ እንመርጣለን።

<u>ማጠቃለያ</u>

ጄኔራል ኃይሌ ባቀረቡት ባለ 28 ገጽ ፅሑፍ ውስጥ የሚተችባቸው እጅግ በርካታ ነጥቦች ቢኖሩም፣ አጠቃላይ መልእክቱ የትግራይ ህዝብን እንደ ህዝብ በሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ እንዲጠላ ለማድረግ ያለመ በመሆኑ የተወሰኑ ነጥቦችን ጠቅሰን የበኩላችንን ትችት አቅርበንበታል። ከዚህም ሌላ ህዝብን እንደህዝብ ለማስጠላትና ከወገኑ ለመነጠል የሚደረገው ሙከራ ሊያስከትለው የሚችለው ጠንቅ ከወዲሁ መገንዘቡ አገራችንን ከውድቀት ያድናታል ብለን እናምናለን። በተጨማሪም አንድን ህዝብ የትግሉ አጋርና የዓላማ ደጋፊ ማድረግ የሚቻለው የያዝነው ዓላማ ለህዝቡ ሊያመጣለት የሚችል በጎ ለውጥ በተግባርና በቴዎሪ በማሳየት እንጂ "በአሳይሁ-አለሁና" ቡራ ከረዮ ባዶ ፉከራ ሊሆን ፈጽሞ አይቻልም ብለን ከልብ እናምናለን። በመሆኑም ዘርን ከዘር ጋር ለማባላት የሚራወጡ ወገኖች ህወሓት/ኢህአዴግን እንደምንታገለው ልንታገላቸው ይገባል። ነገ ህወሓት/ኢህአዴግ ተወግዶ እነዚህ ዓይነቶቹ ጽንፈኞች ሥልጣን ቢይዙ ኢትዮጵያ የሚደላትና ትግል የሚያቆም የሚመስላቸው ወገኖች ካሉ እጅጉን የዋሆች ናቸው። የህዝቦች ጥያቄ በቅጡ እስካልተመለሰ ድርስ ትግል ይቆማል ብሎ መገመት ጅልነት ይሆናል።

ከዚህ በተቀረ ህዝባዊ ትግሉን እግቡ ለማድረስ የሚከተሉት 5ት ምዕራፎች መታለፍ አለባቸው ብሎ ት.ዴ.ት ያምናል። እነሱም፣

1. የአገር ወዳድ ዴሞክራቶች ዓላማ፤ አምባገነናዊውን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በማስወገድ ህዝብ ራሱ የሚቆጣጠረው ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲዋቀር፣
2. ይህንን የጋራ ሀገራዊ ዓላማ ለማሳካት ጥምረታዊ አደረጃጀት ስለሚያስፈልግ አንድ የጋራ መእኸል ባስቸኳይ እንዲቋቋም፣
3. ይህ የጋራ ጥምረት ትግልን በአንድ ማእከል አሰተባብሮ የሚመራ፣ የህወሓት/ኢህአዴግን አገዛዝ በማስወገድም የጋራ የሽግግር የጥምር መንግሥት የመመስረት ዓላማን ያሰቀመጠ እንዲሆን፣
4. ይህ የጥምረት የሽግግር መንግሥት ህዝባዊ ሕገ-መንግሥትና በዚህ ላይ ተመርኰዞም የምርጫ ሕጎችን የሚነድፍ፣ በመጨረሻም ፓርቲዎች የየራሳቸውን ዓላማ አንግበው በመወዳደር አሸናፊው ሥልጣን እንዲረከብ የሚያስችል እንዲሆን እንዲደረግ፣
5. እዚህ ለመድረስ ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያቀራርብ፣ የሚያፋቅርና አብሮ በጋራ የሚያታግል ቅስቀሳ ላይ ማተኰር እንጂ እንደ ህወሓት/ኢህአዴግ መከፋፈል የሌለበትን ህዝብ የሚበታትን እንዳይሆን መስራት፣ ይሆናሉ።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!
ውድቀት ለዘረኞችና በታኞች!!!

ት.ዴ.ት ነሓሴ 2001 ዓ.ም